ቱሳ የኢትዬጵያ ትንሳኤ ድሞክራሲያዊ ድርጅት

Tussa Ethiopian Salvation Democratic Orgaization

# *የህወኃት/ኢህአዲግ አገዛዝ የጠራውን የእርቅና ሰላም ውይይት አስመልክቶ ከቱሳ የኢትዬጵያ ትንሳኤ ድሞክራሲያዊ ድርጅት የተሰጠ መግለጫ*

February 4,2017

ቱሳ የኢትዬጵያ ትንሣኤ ድርጅት በኢትዬጵያ አንድነት ፅኑ እምነት ያለው ብሔራዊ ድርጅት ነው! ቱሳ ማለት በወላይትኛ ምሰሶ ወይም ዋልታ ማለት ሲሆን ህዝቡ ለኢትዬጵያ አንድነት ቀንዓይ እንደመሆኑ ዛሬ አገራችን በምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ከሌሎች መሰል የድሞክራሲ ኃይላት ጋር ለኢትዬጵያ ትንሤኤ የሚታገል አጋር ድርጅት መሆኑን ለማመልከት ነው፤
ቱሳ በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ January 13 እና 14 በተካሄደውና በርካታ ድርጅቶች በተገኙበትና በአሳሳቢው የአገራችን ወቅታዊ ጉዳዬች ዙሪያ በተካሄደው የሁለት የቀናት የምክክር ጉባኤም ባለድርሻ አካል ሲሆን በዚህም የኢትዬጵያ አገር አድን የቀውጢ ጊዜ ግብረ ኃይል ከመሰረቱ ዘጠኝ የአንድነትት ድርጅቶች አንዱ ነው።

እናት አገራችን ኢትዬጵያ በ1960ዎች የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት ሕዝባችን የፊውዳሉ ሥርዓት አንገሽግሾት ለውጥ በመፈለጉ መሬት ለአራሹ የሚል መፈክር  አንግቦ ከዳር እስከዳር በመንቀሳቀሱ አፄው የሚኒስትሮች ሹም ሽር በማድረግ የሕዝብን ትግል ለማብረድ በርካታ ማማለያ ሙከራዎች ቢያደረጉም የኢትዬጵያ ህዝብ ከዳር እስከዳር እንቢኝ በማለት ጭራሽ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ  አያጣፍጡ በማለት በተጋጋለ ስሜት በመንቀሳቀስ የአፄውን መንግስት እንዲያከትም አድርጓል።ሆኖም ከህዝባዊ ዕምቢተኝነቱ ባሻገር በወቅቱ ሁነኛ የተደራጀ ሃይል ባለመኖሩ ወታደራዊ አገዛዝ ስልጣን በመያዝ ለአሥራ ሰባት ዓመታት በህዝባችን ጫንቃ ላይ በመሆን በጉልበት ስገዛ ኖሮ በስተመጨረሻ በዉስጥም በዉጭም የሕዝብ ብሶት በመበራከቱ ሳይወድ በግድ ስልጣኑን ለቋል ::

በቀጣይም እንደባለፈው "ብሶት የወለደው "በሚል ጠመንጃ አንግቦ የመጣው ወያኔ ትግራይን ለመገንጠል በነበረው ህልም በጂኦ ፓለቲካው ሁኔታና በባዕዳን ድጋፍ በለስ ቀንቶት የመላውን ኢትዬጵያ መንበረ ስልጣን ስይዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት 26 ዓመታት ያተረፈዉ ግድያ ፣ እስር ፣ እንግልትና ዘረኝነት ነው ። እንዲየያዉም መሬት ላራሹ መፈክር አንግቦ ለሕዝብ ክብር የሕይወት መስዋዕት ከፍሎ ያስገኘውን ድል በመንጠቅና ወደ ጎን በማድረግ መሬት የመንግስት ነው በማለት ከረጅም ጊዜ ጉልተኝነት የተላቀቀውን ገበሬ ከመሬቱ እያፈናቀለ በሚልዬኖች የሚከራዩ ሕንፃዎችን ለራሳቸውና ለካድሪዎቻቸዉ በመሓል ከተማ እየገነቡ ያከራያሉ ፣ ይንደላቀቃሉ ፤ ይኽው ምዝበራና ዘረኝነት አንሶ ወገኖቻችንን ለጅምላ እስር  ፤ እንግልት ፤ ለሞትና ለስደት እየዳረገ ያለዉን የህወኃት ኢህአዴግ ሰቆቃና ግፍ ያንገሸገሸው ሕዝባችን እንቢኝ በማለት በኦሮሚያ ፣ በደቡብ ኮንሶናቁጫ የመረረ ህዝባዊ እምቢተኛነት ትግል ሲያደርግ ምሬቱ የበዛበት ፣ ጨቅላ ልጆቹን ያጣውና ማንነቱን የተነጠቀው  አማራ

ው ወገናችን ብረት በማንሳት የሞት ሽረት ትግል በማካሄድ ስልጣን የሰፊው ህዝብ መሆኑን በማስረ ገጥ ወደኃላ ላለመመለስ ቆርቶ እየታገለ ነው ፤ አገዛዙም ይህን ን በየቦታው የተዛመተውንና ህዝባዊ እምቢተኝነትለሥልጣኑም አስጊ እየሆነ በመምጣቱ የአስቸኳይ ጊዜ በማወጅ ይህንንም ሽፋን በማ ድረግ ፀጥታን በማረጋጋት ሰበብ ህዝባችን ላይ የጅምላ እስርና እርምጃ በመውሰድ እምቢተኝነቱን ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥር ስር ለማዋል ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ላይ ይገኛል ።

ከዚህም አልፎ ይህንን ጊዜ ለመግዛት መልካም አስተዳደርና ሙስና መንስኤው አድርጎ በመ ሳል ስር ነቀል ጥያቄውን በተኃድሶ ስም ለማርገብ ብዙ ሙከራዎች አድርጓል ፣ ነገር ግን በዚህ ሁኔ ታ ውስጥም አሁንም በርካታዎችን በቁጥጥር ስር ከማዋሉም ባሻገር ዛሬም አንጋፋ መሪዎችን ጭ ምር በሽብርተኝነት ስም በየማጎሪያ ቦታዎች በማስገባት ላይ ይገኛሉ።

አሁንም በአንድ በኩል ህዝቡን በማፈንና በማሸማቀቅ በሌላ ጉኑ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ሰ ላማዊ የድርድር እፈልጋለው በማለት ሰበብ በአምሳያው እንደአሸን የፈበረካቸውን የፖለቲካ ፓርቲወ ችን ጭምር በመጋበዝ ውይይት መጀመሩን ድርጅታችን በአፅዕኖት በመከታተል ላይ ይገኛል ፤ ማን ም ወገን እርቅና ስላምን ሊቃወም አይችልም! ነገርግን በርካታ ወገኖቻችን በጠራራ ፀሐይ በጥይት ተቆልተዋል ይህ ከምርጫ 97 እነ ሺብሬን ጨምሮ ብዙዎች ለስር ነቀል ለውጥ ህይወታቸውን ከፍለ ውበታል እየከፈሉም ይገኛሉ፤ “ባለ ራዕይው መሪ  የነበሩት ሟቹ አቶ መለስ ዜናዊ ለሥርዓት ለውጥ ቋፍ ላይ የደረሰውን የአዲስ አበባን ህዝብ ህዝባዊ ማዕበል ከሰማይ በታች በምንም ጉዳይ ልንስ ማማ ፈቃዳችን ነው በማለት ይህንን ሁሉ የህዝብ አልገዛም ባይነትን ትግል ጊዜ በመግዛት የቅንጅ ት መሪዎችን ለጅምላ እስር በመዳረግ ህዝባዊ ማዕበሉን በማፈን እነሆ ይህንን ትግል በህወኃት መ ሪነት ለአስራ ስድስት ዓመት እድሜ ሰጥተነዋል ፤

ዛሬም ደግሞ ከዚያን ጊዜ በላይ በብዙ ሺዎች በጅምላ ታፍሰው ታስረዋል በሺዎች ለጋ ወጣ ቶች የህይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል እየከፈሉም ነው ስለሆነም ይህ የተጀመረው ውይይት ከጥገ ናዊ ለውጥ ተላቆ ዘላቂ ሰላም ፣ ዕድገትና መረጋጋት የሰፈነባት እናት አገር ትኖረን ዘንድ ሁሉንም ባ ለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ የሽግግር መንግሥት ወይም አንድ የባላደራ መንግሥት መመስረትና በቀ ጣይም የዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ከአንድ ገዥ መዳፍና ቁጥጥር ስር በማላቀቅ በነፃነት በአዲስ በ መገንባት በነፃና ዴሞክራሲያው የምርጫ ሂደት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ብቸኛው መን ገድ ሊሆን ይገባል ፤

ይህ ባልሆነበት ካለፈው ታሪካችን ሳንማር ዛሬም ጥገናዊ ለውጥ እናት ሃገራችንን ከተመሳሳይ የህ ዝብ እልቂትና አፈና የማያከትም ይልቁንም የህዝባችንን ትግል እንዲነጠቅ የሚያደርግ በመሆኑ በአ ገር ቤት የሚገኙ የህዝብ ወገን የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅድመ ምክክር በማድረግ በተወከሉ የጋራ ተወካዬች አማካይነት ለዘላቂ ለውጥ እንዲደራደሩ ጥሪ እናደርጋለን ።

ድል ለኢትዬጵያ ህዝብ!

ቱሳ የኢትዬጵያ ትንሣኤ ድሞክራሲያዊ ድርጅት

Phone USA 1+2022814459

Tussa Ethiopian Salvation Democratic Organization/ Email  tassaethiopia@gmailil.com